# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 43

ታህሳስ 2 ቀን 2015 ዓም (11-12-2022)

የሰሞኑን አገር እንዴት ሰነበተች ቅንብራችንን የምንጀምረው ባለፈው እሁድ በህዳር 25ቀን ከሰዓት በኋላ በተረኛው የኦሮሙማ መሪ በአብይ አህመድ ተመርቆ በተከፈተው የመኪና መጠለያ ሲሆን በዚህ ምረቃ ላይ የሥርዓቱ ቁንጮዎች በሙሉ ተገኝተዋል።ለዚህ የመኪና መጠለያ የወጣው ወጭ በቢሊዮን ይቆጠራል።በዚሁ እለት በወለጋ ክ/ሃገር ውስጥ ከሚኖሩት ንጹሃን ዜጎች ቁጥራቸው ከሁለት መቶ በላይ የሆኑ የአማራ ተወላጆች፣ህጻናትና ሴቶች፣አሮጊትና ሽማግሌዎች በማነታቸው ተለይተው በአንድ ጀንበር ከዬመኖሪያ ቤታቸው ታድነው ተጨፍጭፈዋል።ለነሱ የመቃብር ቦታ ተነፍጓቸው ለጅብና ለዱር አውሬ በተጣለበት አገር ላይ ነው ለመኪና መጠለያ ሲባል ያ ሁሉ ገንዘብ የፈሰሰው። ሌላው ቀርቶ በመንግሥት ተብዬው የዜና አውታር ወንጀሉ አልተገለጸም።የሁሉም ትኩረት በዚሁ የመኪና መጠለያ ምረቃ ላይ ነበር። ከፐላኔቷ ካሉ አገራት ውስጥ የሰው ህይወት ከመኪና ምቾት በታች የሆነባት አገር ብትኖር የኛይቱ ኢትዮጵያ ነች።አዎ የሚያብለጨልጭ የፈረንጆች ዕቃ ብርቅ የሆነበት፣ በባዶ እግሩ ሲኳትን ያደገ የጎሰኞች ቡድን ከሰው ልጅ ህይወት በላይ ለመኪና ክብር ቢሰጥ የሚያስደንቅ አይሆንም።

በዚሁ ምረቃ ላይ የታዘብነው ቢኖር የጋራዡ መግቢያና መውጫ ምልክቶች በእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቻ መጻፋቸውን ነው።99% በላይ የከተማዋ ነዋሪ በሚናገርበትና በሚገባው፣ብሎም የመንግሥት አስተዳደር ቋንቋ ነው ተብሎ የሕግ እውቅና በተሰጠው የአማርኛ ቋንቋ አለመገለጹ በአማርኛ ቋንቋና በአማራው ላይ ያላቸውን ጥላቻና የማራከስ ዘመቻ በግልጽ የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ ጸረ ኢትዮጵያ አቋም ነው።ከዚያም ባለፈ በግድ ለመጫን ላሰቡት የቁቤ ፊደል የማመቻቸት ስልት ሆኖ አገኝተነዋል። ያሰማሩት ገዳይ ቡድን በገጠር አማራውን ይጨፈጭፋል፣ሌሎቹ በከተማ የአማራውን ብሎም የኢትዮጵያዊነትን እሴት ያጠፋሉ። በሌላዎቹ በሰለጠኑት አገሮች የመኪና ጋራጆች አቅጣጫ ምልክት የሚገለጸው በአገራቸው ቋንቋ ሲሆን በተደራቢም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ይብራራሉ።ለመሆኑ ከአማርኛ በቀር ሌላ ፊደል ያልቆጠረው መኪና አሽከርካሪ ምን ይውጠው ይሆን? ሁኔታውን ለጠጥ አድርገን ብናዬው ይህ ጉድጓድ ከመኪና ማቆሚያም በላይ ለሆነ ደባ ሊያገለግል እንደሚችል መረዳት ይገባል። በመጀመሪያ ቦታውን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እጅ በመንጠቅ የመስቀል በዓል ሲከበር ከባቢውን የሚያውደውን የቅዱስ ማጠንቱን አውድና ክብረ በዓል በመኪና ጭስ ተክቶ በመበከል ክብሩን ማራከስ ሲሆን አሁን የተቀዬሰው ከተማዋን የመዋጥ ዕቅድ ከተሳካ ከእንግሊዝኛው ጎን በቁቤ መጻፉ የማይቀር ደባ እንዳለ እርግጠኞች ሆነን መናገር እንችላለን።ምናልባትም ይህ ለመኪና ማቆሚያ ተብሎ የተሠራ ዋሻ የመጨረሻ ከተማዋን የመዋጥ ትግል ሲደረግ የኦነግ ጦር ምሽግ ላለመሆኑ ዋስትና የለም።

በተመሳሳይም በዬትምህርት ቤቱ ተማሪው በቁቤ የተጻፈ የኦነግ መዝሙር እንዲዘምርና የኦነግን ባንዲራ እንዲሰቅል ማስገደዱ ለወደፊቱ ዕቅድ የመለማመጃው ጅማሮ መሆኑን ሁሉም ልብ ሊለው ይገባል።የኦሮሞ ክልል ናቸው በሚባሉት ቦታዎች ዋናና ብቸኛ የሥራ ቋንቋ ሆኖ ኦሮሞ ላልሆነው ነዋሪ ዜጋ ፈተና ከሆነበት ውሎ አድሯል።እንደሚከተሉት ሕገ ጥፋትማ ቢሆን አማርኛ አንዱና ዋናው ቋንቋ ነበር። ከዚህ አይነቱ ግዳጅና ዓይን ያወጣ የተረኝነት ድፍረት ለመገላገል ያለው ብቸኛ አማራጭ የግድ የሰፈነውን ጸረ ኢትዮጵያ የሆነ ሥርዓት ማሶገድና ፍጹም ኢትዮጵያዊ የሆነ ፣ከጎሰኝነት የጸዳ ስርዓት ማስፈን ብቻ ነው።

በማግስቱ ሰኞ በህዳር 26 ቀን ቀደም ሲል መምህራን ላቀረቡት የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ መልስ የማያገኙ ከሆነ የሥራ ማቆም አድማ እንደሚመቱ ባሳለፉት ውሳኔ መሠረት ከሃያ በላይ በሚሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በሚያስተምሩት መምህራንና በተማሪዎች ተባባሪነት አድማው ተካሂዷል። አሁንም በሌሎቹ ዩኒቨርሲቲዎች ተስፋፍቶ ከአርባ በላይ ዩኒቨርሲቲዎች አድማውን ተቀላቅለዋል። ከአድማው በፊትም ሆነ አድማውን ተከትሎ መምህራንን ማሳደዱ ተጠናክሯል።ብዙዎች ታስረው ዩት እንደደረሱ አልታወቀም። ይህንን የዴሞክራሲያዊና የሙብት ጥያቄ ከአገር ክህደት ጋር በማስተሳሰር የተቃወሙ የሥርዓቱ ደጋፊዎች አልጠፉም።በተለይም የመምህራኑን ሙብት ያስከብራል ተብሎ የተቋቋመውና የሚጠበቅበት የመምህራኑ ማህበር በተረኞቹ መዳፍ ስር በመውደቁ የመምህራኖቹን ጥያቄ ተቃውሟል። አገር የኤኮኖሚ ቀውስ ውስጥ በገባችበት ወቅት ላይ መነሳት የሌለበት ጥያቄ ነው ብሏል።ይህ አድርባይ ማህበር በቢሊዮን ብር የተሠራውን ጋራጅና ወደፊትም በ500 ቢሊዮን ብር ወጭ ሊሠራ የታቀደውን የአብይ አህመድን ቤተመንግሥት ግንባታ የእድገት ማሳያ አድርጎ አድንቆ ተቀበለው እንጂ አገር ባለችበት የኤኮኖሚና የፖለቲካ ቀውስ ወቅት መገንባቱ ሳይሆን መታሰቡ ተገቢ አይደለም ለማለት አልደፈረም።ቢሊዮን የማያወጣውን የመምህራን የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ ግን ሸንጡን ገትሮ ተቃውሟል።እንዲህ ነው ዓይን ያወጣ አድርባይነት፣ከገሙ አይቀር ብስብስ!

የሚገርመው ነገር ከ40% በላይ የሚሆነው መምህር የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ደጋፊና አባል መሆኑ ነው።ይህንን ስናይ ወደሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽ አይከፋሽ ለማለት እንወድና ግን መሳሳት ከሰው ልጆች ድክመት አንዱ መሆኑን በማወቅ አልፈነዋል።አሁን ጥያቄው ከደመወዝ በላይ ነው።የአገር አንድነትና ሰላም፣የሕዝብ ሙብት መከበርና የዴሞክራሲ ስርዓት መስፈን ስለሆነ ከራሳቸው አጥር ወጥተው አገር አቀፍ ለሆነው ጥቅምና ጥያቄ እንዲሰለፉ ጥሪ እናደርጋለን።ደመወዝም እኮ ከጥቅም ላይ የሚውለው አገርና ሰላም ሲኖር ነው! ሰላም ከጠፋ፣የጎሰኞች ስርዓት ከቀጠለ ሚሊዮን ብር ተሸክመው አንድ ዳቦ ገዝቶ ለመብላት የማይችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል።ሰላምና አንድነት ካለ ደግሞ ደሃ ሰውም ቢሆን በአቅሙ ገዝቶም ብቻ ሳይሆን ለምኖ ለመብላት ዕድል ይኖረዋል።

በዚሁ መምህራን አድማቸውን በጀመሩበት ቀን አብይ አህመድ ለማደናገር ሲል አጃቢዎቹ ከሆኑት መሃል ብርሃኑ ነጋን፣ ዳንኤል ክብረትንና ሌሎቹን አስከትሎ የምሑራን ውይይት በሚል ሰበብ አንድ መድረክ ከፍቷል።በዚህ ስብሰባ ላይ አብይ አህመድ እኔ የተሰጠኝን ሃላፊነትና የገባሁትን ቃል ኪዳን ለማክበር ሞክሬአለሁ፤ከስምንት ሰዓት በላይ እስከ አስራስድስት ሰዓት ድረስ እሰራለሁ በማለት ተጠያቂነቱን በሌሎች ላይ ሲደፈድፍ ተደምጧል።ጥያቄው እረጅም ሰዓት ወንበር ላይ መቀመጡ ሳይሆን ምን ጥሩ ነገር ሰራ የሚለው ነው። እንደኛ ከሆነ አገር የሚያፈራርስ ሴራ እንጂ ለአገር የሚበጅ፣የሕዝቡን ጥያቄ የሚመልስ፣የአገር አንድነት የሚያስከብር፣ለሰላም የሚያበቃ ሥራ ሰርቷል አንልም።ከ16 ሰዓት አገር የማፍረስ ሴራ ይልቅ የግማሽ ሰዓት ለአገር ሰላምና ለሕዝብ ደህንነት ተግባር ላይ የሚጠፋ ጊዜ የበለጠ ጥቅምና ዋጋ ይኖረዋል።

ከተሰበሰቡት ውታፍ ነቃይ መምህራን በኩልም አንዱ ዶር ተብዬ ሲናገር “መምህራን እንደ ኤስያና ምስራቁ ዓለም መምህራን ለአገራቸው እድገት መሥራት አለባቸው፤እነዚያ አገራት ያደጉትና የበለጸጉት መምህራኑና ሕዝቡ ለጊዜያዊ ችግር እጅ ሳይሰጡ ከመንግሥት ጋር ባደረጉት ትብብር ነው” ሲል ተደምጧል።እርግጥ ነው ለአንድ አገር እድገት የሕዝብና የመንግሥት ትብብር ያስፈልጋል።ጥያቄው ግን ምን አይነት መንግሥት ጋር ነው ትብብሩ የሚል ነው።ይህንን ሃሳብ የሰነዘረው መምህር ያልተገነዘበው ቢኖር በጠቀሳቸው አገሮች ውስጥ የጎሳ ፖለቲካና ሥርዓት እንዳልሰፈነና ሁሉም በአንድ አገር ዜግነት መንፈስ እንደሚኖር ነው።መቼም በአገራችን ምሁርነት ትርጉሙን አጣ እንጂ ትክክለኛ ምሁር ቢሆን ኖሮ የተያዘው መንገድ እንደ ኤስያ አገሮች ለዕድገት ያበቃል ሳይሆን እንደ ዩጎዝላቪያና ሩዋንዳ

ለእልቂትና ለመበታተን ይዳርገናል ብሎ ያስጠነቅቅ ነበር።በነዚህ አይነቶቹ መምህራን የልብ ልብ የተሰማት የአነጓ ከንቲባ አዲስ አበባ የኦሮሞ ዋና ከተማ ነች፤ነዋሪውም በሁሉም ቦታ የኦነግን መዝሙር መዘመርና ባንራውንም መሸከም አለበት የሚል ትእዛዝና ማስጠንቀቂያ በይፋ አስተላልፋለች።ይህች ጉደኛ ያሩሲ ቁሮ የአዲስ አበባን ታሪክና የነዋሪውንም ስነልቦና ያላወቀች ትእቢት ያወራት፣ዘረፋ ህሊናዋን የነሳት ለመሆኑ ከዚህ በላይ ማስረጃ የለም። የተማሪውንና የመምህራኑን ተቃውሞ የፋኖ አክራሪና የምዕራባውያን ሴራ ውጤት ነው በማለት ከወያኔ ጋር ተናንቆ ለስልጣኗ መቀጠል በራሱ ስንቅና ትጥቅ መስዋእት የከፈለውን የአማራ ፋኖ አሸባሪ በማለት ተሳድባለች።ውለታ ቢስ!ምዕራባውያኑም ቢሆኑ ከአብይ አህመድ መንግሥት የበለጠ አሸከርና አገልጋይ የላቸውም። አማራውን ለማጥፋትና ኢትዮጵያን ለመበታተን የሚቀርባቸው የጎሰኞቹ ሥርዓት ነው።ለዚያም ነው ለወያኔ ሽንጣቸውን ገትረው ሲከራከሩ የአማራውን መጨፍጨፍ በዝምታ ያለፉት።የወልቃይትና ጠገሌን የራያና አዘቦን የአማራውን አጽመ-እርስት ምዕራብ ትግራይ እያሉ ለመንጠቅ የሚረዳ ቅድመ እውቅና የሚሰጡት።

የትምህርት ሚኒስቴር ተብዬውም የግም ሞት ሰባቱ መሪ ብርሃኑ ነጋ በመምህራኑ ጥያቄ የተነሳ ከ12,000(አስራሁለት ሽህ) በላይ የዩኒቨርስቲ ምሁራንን ለማባረር ማቀዱን ባለፈው ዝግጅታችን ገልጸናል።ይኸው ጉደኛ የተማሪዎችን ተቃውሞ ተከትሎ በአዲስ አበባና በተለያዩ ቦታዎች የተቀሰቀሰውን የሕዝብ ተቃውሞና የመንግሥትን ሴራ በማዬት የሚሰነዘረውን ትችት ውድቅ ለማድረግና የራሱንም የሥልጣን ወንበር ለማስከበር ሲል “መንግሥት የለም የሚሉ አሉ፤መንግሥት ግን አለ፤ ይህንን የሚሉት በግርግር ሥልጣን ለመያዝ የሚፈልጉ ናቸው”ብሏል።እኛም የምንሰጠው ምላሽ መንግሥት ብለን የምንጠራው በሕዝብ ምርጫ የተሾመ፣ የሕዝብን መብትና ደህንነት፣ያገርን ሰላም፣ልዑላዊነትና አንድነት የሚያስጠብቅ ሲሆን ነው።ከዚያ ውጭ በጉልበትም ሆነ በአሻጥር ሥልጣን ላይ የተቀመጠም ሆነ ሌላ አገር አጥፊ ጎሰኛ ስብስብ ሥልጣን ላይ ቢቀመጥ መንግሥት ነው አንልም የሚል ነው። በኢሕአዴግና በብልጽግና ተብዬዎቹ መካከል የአቋምና የፖለቲካ ልዩነት እንደሌለ ሁሉ በብልጽግናና በኦሮሞ ፍደራሊስት መካከል ልዩነት የለም።ሁሉም ከአንድ ከጸረ ኢትዮጵያ ምንጭ፣ከኦነግ ቦይ የሚቀዱ የጥፋት ቡድኖች ናቸው።

የአብይ አህመድ ጉደኛ ስብስብ በጉያው ደመወዝ ቆርጦ፣ ውድ መኪናና ሴኩሪቲ መድቦ፣በቪላ ቤት እያሽቀረቀረ ያስቀመጣቸው በቀለ ገሪባ፣ጁዋር ሞሃመድ፣ዳውድ ኢብሳንና የመሳሰሉትን የአሸባሪው ቡድን መሪዎች፣በአደባባይ “አማራን ጨፍጭፍ ! ነጥለህ ምታው!አብረኸው አትኑር፣ከመሬትህ አሶጣው!አትገበያይ፣አትግዛው፣አትሸጥለት! አትጋባ፣የተጋባህም ተፋታ!የሚል ትዕዛዝ ሲያስተላልፉ በዝምታ ማለፉ የጭፍጨፋው ተካፋይ መሆኑን በግልጽ ያሳያል።እነደ ሌሎቹ አገርማ ቢሆን እንኳንስ በከተማ የሚንጎራደድና ባጀት የተቆረጠለት የሽብር አዛዥ ቀርቶ ለብዙ ዓመታት ተሰውሮ የቆዬ ቢሆን ከፍርድ አያመልጥም ነበር።ለዚህም ምሳሌ የሚሆነን አይሁዶችን ከጨፈጨፉት የናዚ መሪዎች ውስጥ በያገሩ ከ75 ዓመት በላይ ተደብቀው የኖሩ ታድነው ለፍርድ መቅረባቸውና በቅርቡም በሩዋንዳ ጭፍጨፋ ላይ በራዲዮ ጣቢያ የቀሰቀሰ ግለሰብ ተሰውሮ ለሃያ አምስት ዓመት ከተደበቀበት የፓሪስ መንደር ተይዞ ለዓለም ፍርድ ቤት ቀርቦ በዕድሜ ልክ እስራት መቀጣቱ ነው።የኢትዮጵያውያን ደም ግን ከውሃ የቀጠነና የረከሰ ሆኖ መንግሥቱ ሃ/ማርያምን የመሰለ ገዳይ ወንጀለኛና የአሁኖቹም የወያኔና የኦሮሙማ ጨፍጫፊ ወንጀለኞች በሕግ ሳይጠዬቁ በሰረቁት ያገር ሃብት ተዝናንተው ይኖራሉ።ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው በእኛው በኢትዮጵያኑ ድክመት የተነሳ ነው።ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይደርስም ወይም ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም እንደሚባለው ሰሚና ክብር ያጣነው በቁም ነገር አለመሰባሰባችንና ለመብታችን አለመቆማችን ነው።ለአድርባዮችና ለተረኞች መፈንጫ መሆናችን

ነው።በዚያም አልቆመም  በወለጋ የተፈጸመው እጅግ ዘግናኝ ጭፍጨፋ ምህዳሩን አስፍቶ በሌሎቹም ቦታዎች በመፈጸም ላይ ነው።

ጨፍጫፊዎቹ የኦነግ መንጋ ብቻ ሳይሆኑ በመንግሥት የሰለጠኑ፣የታጠቁና የሚታዘዙ የክልሉ ሚሊሽያና ልዩ ሃይል አባላትም ጭምር ናቸው።አልፎ አልፎም የሚሰማው ወሬ በመከላከያ ውስጥ ያሉትም የጎሳ ትስስር ያላቸው መረጃና መሣሪያ እንደሚያቀብሉ ነው።ከጥቃት ያመለጡ ጉዳተኞች በሰጡት ቃል ለመከላከል ስንሞክር የክልሉ ባለሥልጣኖች በወታደር ሃይል ይመቱናል።እኛን እዬገደሉ አሽባሪዎቹን ይሸልማሉ።ከኛው ጋር ያደጉ፣አብረን የበላን የጠጣን ሳይቀሩ እኛን ለማጥቃት  ቆንጨራና ገጀራ ይዘው ተሰልፈዋል።ስንኖር ምንም አይነት ሃጢያት አልሰራንም፤ማንንም አልበደልንም። ቋንቋቸውንና ባህላቸውን አክብረን ኖረናል።ተጋብተን ተዋልደናል፣መስጊድና ቤተክርስቲያን አብረን ጸልዬናል።እንደ ጥፋት ቢቆጠርብን በትጋት ሠርቶ ማደራችንና እራሳችንን መቻላችን ነው።ያለንንም ቢሆን አካፍለን  እንጂ ብቻችንን አልበላንም።ሲሞቱ ቀብረን፣ሲታመሙ ጠይቀን ፣ሲያገቡ ደግሰን፣ከፉ ደጉን ተካፍለን ኖረናል፣ልጆቻችን  ከልጆቻቸው ጋር አብረው ተጫውተው አድገዋል፤ለቁም ነገር በቅተዋል።ከሁለት ትውልድ በላይ ተወልደን ያደግነው በኖርንበት ቦታ ነው፤ሌላ ቦታ የለንም። ወላጆቻችን በኢትዮጵያዊነታቸው ምክንያት እዚህ ለመኖርና እኛን ወልዶ ለማሳደግ ችለዋል፤እኛም ወልደን አሳድገናል።በማሳደግም ላይ ነን።የነሱ ልጆች በኢትዮጵያ ምድር ቀርቶ በውጭ አገር ይኖሩ የለም እንዴ?አዘሮ የማዬት ህሊና ለምን አጡ?ሲሉ በምሬት ይናገራሉ።እውነትም ሕሊና የማጣት እብደት ነው።በአሜሪካና በአውሮፓ አገር ተሰዶ የሚኖር የኦሮሞ ተወላጅ በገዛ አገሩ በኢትዮጵያ መሬት ላይ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ከአገሩ  ይውጣ ብሎ  ለጨፍጫፊዎቹ ድጋፍ ሲሰጥ ማዬትና መስማት በኦሮሞ ተወላጆች ላይ የተፈጥሮ ወይም ያስተሳሰብ ጉድለት አለ ብሎ ለመገመት ይገፋፋል። በሚኖሩበት የፈረንጅ አገር ያለ ዘረኛ እያደነ ቢፈጃቸው ምን ይሰማቸው ይሆን?ህሊና ቢሱ የአክራሪው ኦሮሙማ ደጋፊ የተማሪ ቡድን አሁንም ዳውን ዳውን ነፍጠኛ እያለ መጮሁ ነው።በሥልጣን ላይ ያለው የራሱ ጎሳ መሆኑን እንኳን ለመገንዘብ አልቻለም።ይባስ ብሎም  ከመቶ ዓመት በፊት የሞቱትን አጼ ሚኒሊክንም ዳውን ዳውን ምኒልክ እያለ ሲጮህ መስማቱ የድንቁርናውን ደረጃ ያሳያል።በመስቀል የደነቆረ አበባዬሁ ወይ እንዳለ ይሞታል ያልነውም ለዚያ ነው።ምን ያድርግ አፍ የፈታውና ከኦነጋውያን የቀሰመው እውቀት ነፍጠኛና ሚኒሊክ የሚለውን ቃል ብቻ ነው።

በወለጋ፣በአርሲ፣በሐረር፣በባሌ፣በጅማ፣በኢሉባቦር፣በሸዋ የሚኖረው የኦሮሞ ተወላጅ በስሜ አትነግዱ!ለምንስ አማራው ይጨፈጨፋል?ብሎ ድምጹን አላሰማም።እንደመንጋ የሚነዱት ልጆቹ አደባባይ ወጥተው አማራ ነፍጠኛ፣አማራ ይታረድ!ይጨፍጨፍ!ሲሉ አልተቆጣም።ጥቂት ደፋርና ሰብአዊነት የሚሰማቸው፣በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑና የሚኮሩ፣የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተካታዬ የሆኑ የኦሮሞ ልጆች እንደከሃዲ ተቆጥረው ከአማራው እኩል ተጨፍጭፈዋል፤ እዬተጨፈጨፉም ነው።ይህ የአማራውንና  የኦሮሞውን አንድነት የሚያጠናክር ትልቅ ምልክት ነው። የሌሎቹም ጎሳ ተወላጆች ይህንን ፈለግ ተከትለው አገር አድኑን ትግል ሊቀላቀሉ ይገባል።በዝምታ እንተርፋለን ብለው ከሆነ  በጅብ ተለያይተው የተበሉትን የአራቱን በሬዎች ታሪክ አስታውሱት እንላለን።

አገር ወዳዱ አማራ ግፍና መከራው ሲበዛበት፣ ችሎ ችሎ ሲመረው እራሱን ከአደጋ ለማዳን የመከላከል እርምጃ መውሰድ ሲጀምር ብርክ ውስጥ የገቡት የኦነግ መንጋዎች ከፓርቲ እስከፓርላማ ባለ መድረክ ላይ ያዙን ልቀቁን በማለት ላይ ናቸው።ላለፉት ዓመታት አማራው ሲጨፈጨፍ ለምን ያላሉት የኦሮሞ ብልጽግና የፓርላማ ተመራጮች አሁን ላይ አሸባሪውን የኦነግን ቡድን ለድርድር ይቅረብ እያሉ በመጮህ ላይ ናቸው።ወንጀለኛ በሰራው ወንጀል ይቀጣ የሚል የሕግ አውጭና አስከባሪ ሚናና

ሃላፊነት የተሸከመ የፓርላማ አባላት በዚህ አይነቱ ጸረ ፍትሕ ተግባር ላይ ሲውሉ ማዬት የሥርዓቱን መበስበስ በግልጽ ያሳያል። ሌላው ልማደኛው የአሸባሪዎች መሪ የሆነው ጁዋር ሞሃመድ በበኩሉ በኦሮሚያ ውስጥ አማራ ታጥቆ የመከላከል መብት የለውም ብሏል።በሌላ አባባል አማራው የመጨፍጨፍ ግዴታ አለበት ማለቱ ነው። በነዚህ የኦሮሞ ጸረ ኢትዮጵያውያን የሚረጨው መርዝ እስካሁን ለደረሰው ጥፋትና እልቂት ምክንያት ስለሆነ በሕግ ሊጠዬቁ ይገባል።ወንጀለኛና አሸባሪ፣ ለዚያውም የሕጻናትን ህይወት የቀሰፈ በነጻ የሚለቀቅበት ሕጋዊ መስፈርት የለም። ሊኖርም አይገባም። የዘር ጭፍጨፋና ያገር ክህደት የፈጸመ በእስር ቤት እንጂ እንደ ሰላማዊ ታጋይ በድርድር ጠረጴዛ ላይ ሊቀመጥ አይችልም።

አማራውን በማጥቃቱ ላይ የተሰማሩት ወያኔ፣ አክራሪ ኦነጋውያንና ኦሮሙማዎች ብቻ አይደሉም ፣ ላለፉት 32 ዓመታት ለነዚህ ጸረ ኢትዮጵያ ቡድኖች ኢጋሰስ ሆኖ ያገለገለው በአማራ ስም የተቀመጠው ብአዴን የተባለው ስብስብ ጭምር ነው። ይህንን ተላላኪ ጭምር ነጻ ሊያደርገው የተነሳውን የአማራ ፋኖ እያደነ በመግደል፣በማሰርና ትጥቅ በማስፈታት ሥራ ላይ ተጠምዷል።ለዚያም ነው ደግመን ደጋግመን

ጠላትማ ምን ጊዜም ጠላት ነው፣

አስቀድሞ መምታት አሾከሿኪውን ነው።የምንለው።

አዎ! ብአዴን ከወያኔና ከኦነግ ተለይቶ የማይታይ ጠላት ነው!መመታት አለበት። ለኦነግ ወንጀል ተባባሪ በመሆን የሦስት ሚሊዮን ብር ካሳ መክፈሉን ባለፈው ዝግጅታችን ገልጸናል።አሁንም ቢሆን የበለጠ ከመክፈል ወደኋላ አይልም።

ተፈናቃዮቹ አሁንም ቢሆን በመንግሥት ላይ ተስፋ አልቆረጡም። በኖርንበት ቦታ  በሰላም የምንኖርበትን መንገድ ያመቻችልን ወይም  መውጫ መንገድ ይከፈትልን ይላሉ።በእኛ በኩል ግን ጥሎ መሄዱ ለጨፍጫፊውና ለአስጨፍጫፊው ትልቅ ድል ይሆናል።የሚፈልጉትም ቦታውን ከሌላው ኢትዮጵያዊ አጽድቶ ለመገንጠል ያላቸውን ዓላማ ለማሳካት ነው።ስለሆነም ምክራችን እራስን  በቅጡ አዘጋጅቶ  ከጥቃቱ መዳንና የአገርን አንድነት ማስከበር ነው የሚል ነው።ለውሻ አይሮጡም ለጅል አይስቁም የሚለው ምክራችን ነው።ወይም በጀግና ቋንቋ

የምን እዬዬ ነው የምን አንገት መድፋት፣

የምን መኮብለል ነው የምን ጥሎ መጥፋት፤

ቆርጦ መነሳት ነው ገፊውን ለመግፋት፣

እስከመጨረሻው አጥፊውን ለማጥፋት።

ለዚህ ሰብአዊ ግዳጅና አገራዊ ክብር ሁሉም ኢትዮጵያዊ ያሸባሪዎቹን ጎራ ለመደርመስና ለማፈራረስ እጅ ለእጅ ተያይዞ መነሳት አለበት።አሁን ድምጻቸውን በመግለጭ የሚያሰሙ የፖለቲካ ድርጅቶች መሽኮርመማቸውን ትተው ለብሔራዊ ዘመቻ ብሔራዊ የአንድነት(የትብብር መድረክ) ግንባር መፍጠር አለባቸው።ሲጀመር ወያኔ ቀምሮ ኦነግ ኦሕዴድ ተረክቦ ያስቀጠለውን ሕገ ጥፋቱን ተቀብለው የአብይ አህመድን መንግሥት ለማጀብ መሽቀዳደማቸው ጥፋት ነው።ያንን ጥፋታቸውን በይፋ አምነው ይቅርታ መጠዬቅ ይኖርባቸዋል።ሕዝብና አገራቸውን ሊክሱ ይገባል።የፖለቲካ ፓርቲ መሆን ማለት

ቢሮ ውስጥ ተቀምጦ በእራፊ ወረቀት ላይ መግለጫ ማውጣት ብቻ አይደለም።በአስፈላጊው የትግል መስክ ፊት ለፊት መሰለፍንም ይጨምራል።

ትግሉ የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን የመሣሪያም ትግል ነው።የፖለቲካውንና የጦር ሃይሉን በመዳፉ ይዞ በአገርና በሕዝብ ላይ ሴራ የሚጎነጉነውን የተረኞች ቡድን ለማንበርከክና አገርና ሕዝብን ለመታደግ የተቃዋሚው ጎራ በበሰለ የፖለቲካ መስመርና በታጠቀ ወታደራዊ ሃይል በልጦ መገኘቱ ወሳኝ ነው። ድል ምን ጊዜም ከሃለኞች መዳፍ አትወጣም።የአገር አንድነትና የዴሞክራሲ ሥርዓት የሚሰፍነው በጸረ አንድነትና በአንድነት ሃይሎች መካከል በተደረገ እልህ አስጨራሽ ትግልና ጦርነት ነው።ምን ጊዜም የአንድነት ሃይሉ በቁጥርም በዓላማ ጥንካሬም የበላይ ስለሆነ የማታ ማታ ድሉ የርሱ ነው።አሁን አድገውና በልጽገው፣ አንድ አገር ሆነው የምናያቸው አገሮች በዚህ ፈተና ውስጥ ያለፉ ናቸው።አሜሪካ፣ በአንድነትና በጸረ አንድነት ሃይሎች መካከል ውጊያ ተደርጎባት የአንድነት ሃይሉ በማሸነፉ አሁን ላለችበት ደረጃ በቅታለች።ሌሎቹም የአውሮፓ አገሮች እንዲሁ።

መምህሩ፣ነጋዴው፣አርሶ አደሩ፣ተማሪው በየፊናው የሚያደርገው ትግል፣የተበታተነው ሕዝባዊ ተቃውሞ በአንድ ጎራ ሊሰባሰብ ይገባል። የሥር ነቀል ለውጥ ተረግዟል፤ ያንን ማዋለድ የሁሉም ለውጥ ፈላጊ ግዴታ ነው።የስቃይ ድምጽ እያሰሙ ፈጣሪን ከመለመን አንድ ጊዜ ሃይልን ሰብስቦ አምጦ ወልዶ መገላገል ይሻላል።ፈጣሪም ቢሆን የሚያግዘው እውነተኞችንና ግፉአንን ነው።እርዱኝ እረዳችኋለሁ ሲልም የመጀመሪያው ድርሻ የራሳችን እንደሆነ በማሳዬት ነው።ለትግሉ ተስፋ የሚሰጥም ምልክት እያዬን ነው።

የጎሰኞቹ ሥርዓት እዬተፍረከረከ በመሄድ ላይ ነው። ሌባና ሙሰኛ እዬተባባለ እርስ በርሱ ይተራመሳል።አንዳንዱም ከሚመጣው ያመለጠ መስሎት ሥልጣኑን ለመልቀቅ ዳርዳር እያለ ነው። ለአራት ዓመት ፍትህ ስታዛባ የኖረችው ማዕዛ አሸናፊ የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ ማስገባቷ ተሰምቷል፣ እነ አብይም ማን አምልጦ ማን ይቀራል በሚል እልህ ጥያቄዋን ውድቅ አድርጎ ሃሳቧን እንድትለውጥ የሽማግሌ ጋጋታ አሰማርቷል። ሌሎቹም በወጡበት ለመቅረት ሻንጣቸውን እዬከሸፉ ነው።ሲያልቅ አያምር!የእምቧይ ካብ!

ወያኔም በአይተነው ጊዜ ፖለቲካ አንድ እግሩን መቀሌ ሌላ እግሩን ተንቤን በረሃ አንፈራጦ ያገኘውን ይዞ ለመገንጠል አሰልቶ በመጠበቅ ላይ ነው።በአብይ አህመድ መንግሥት ትብብር የሚፈልገውን እስኪያገኝ ድረስ ብቻ ነው የሚጠብቀው።ለይምሰል መሣሪያ አስረከብኩ፣ተዋጊውን ትጥቅ አስፈታሁ ቢልም ጠንካራ ተዋጊውን በስከጀርባ እንዲመሽግ አድርጓል።የወያኔም ሆነ የኦነግ አገር የመገንጠል ዓላማ የሚሳካው የአገር ወዳዱን ኢትዮጵያውያን መዳከምና አንድ አለመሆን ተከትሎ ነው።

ስለሆነም አሁንም እንደ ቀድሞው የሕዝብ ትግል ይቀጣጠል እንላለን።ለድል እንዲበቃም የአንድነት ግንባር ይቋቋም እንላለን። በውጭ አገር የሚኖረው አገር ወዳድና የሥርዓቱ ተቃዋሚ በተበታተነ መልኩ የሚያደርገውን ትግል በአንድ አመራር ስር እንዲያደርገው ጥሪ እናደርጋለን።የጎጥና የመንደርተኛነት ሰልፍ እንዳይበክለው ይጠንቀቅ እንላለን።ሌላው የትግሉን ግለት እያዩ አይተነው ጊዜ ወደሚያዋጣው በሚል ብልጣብልጥ ፖለቲካ የነበሩበትን ጎራ ለመልቀቅ ዳር ዳር የሚሉትንም ታዝበናል።ከነዚያ ውስጥ የግም ሞት ሰባቱ ጀሌ አንዱ ነው።ብርሃኑ ነጋ፣አንዳርጋቸው ጽጌና ኮልኮሌዎቻቸው ከተጠያቂነት ያመለጡ መስሏቸው በሥርዓቱ ላይ ጣታቸውን በመቀሰር ላይ ናቸው። አብይ ያሻግረናል ያሉት ጫጫታ ሁሉ ገደል የገባ ይመስላል።እንደ እስስት እራሳቸውን እዬቀያዬሩ ማጭበርበር ጊዜው ያለፈበት ስልት ስለሆነ እባካችሁ ሞኞችሁን ፈልጉ ለማለት እንወዳለን። እንደልማዳቸው በሕዝቡ ትግል ውስጥ ገብተው እንዳይበክሉ ጥንቃቄ ይደረግ እንላለን።ከልባቸው

የሚጸጸቱ ከሆነ ለፈጸሙት ክህደት ይቅርታ መጠዬቅና ከፖለቲካው ዓለም እራሳቸውን እንዲያርቁ እንመክራቸዋለን።ይህ ማለት በፈጸሙት ሥራ አይጠዬቁ ማለት አይደለም ።ፍርዱን ሕዝብ እንዲሰጥበትም እናሳስባለን። ማንም አቡክቶ አቡክቶ በነጻ የሚለቀቅበት ሁኔታ ማክተም አለበት። አለበለዚያ ፍትሕን ትርጉመቢስ ያደርጋል።

በዚሁ በህዳር የመጨረሻ ሳምንት በትምህርት ቤት ውስጥ የተቀሰቀሰው እምቢ ባይነት ተስፋፍቶ ቀጥሏል።በመርካቶ፣በንፋስ ስልክ---ወዘተ ትምህርት ቤቶች ተማሪው አሻፈረኝ ብሏል።የከተማው የኦነግ ተጠሪም አዳነች አቤቤ በዬቀኑ የድፍረትና የብልግና ግራፏ እዬጨመረ ሄዷል።በውድም በግድም የኦሮሞ ባንዲራ ትሰቅላለህ መዝሙሩንም ትዘምራለህ ብላለች።ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይደፍራል ሆነና ለድፍረቷ ገደብ አጥታለታለች።የኦሮሞ ሕዝብ ባንዲራ ሳይሆን የኦነግ ባንዲራ ነው። መዝሙሩም የኦሮሞ ሕዝብ መዝሙር ሳይሆን የኦነግ መዝሙር ነው።የኦሮሞ ሕዝብማ ከቀሪው ወገኑ ጋር ሲሰቅልና አክብሮት የኖረው አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ነው።ሲዘምርም የኖረው የኢትዮጵያን ብሔራዊ መዝሙር ነው።በዚያ ሥር ተሰልፎ በዬጦር ሜዳው ብዙ መስዋእት ከፍሏል። የኦነግ ባንዲራና መዝሙር ሕጻናትን ለማረድ፣የእርጉዝ ሴትን ሆድ ለመቅደድ፣እውር አዛውንትን ለመግደል የሚፎከሩበት የጥፋት ምልክትና ድምጽ ነው።ከአገር ወዳዱ የኦሮሞ ሕዝብ ጋር የሚያገናኘው የለም።

በዚሁ በህዳር 29 ቀን ላለፉት 28 ዓመታት ጸድቆ በሥራ ላይ የዋለው አገር አጥፊ ሰነድ በአዋሳ ከተማ ብዙ ወጭ በተደረገበት ድግስ ታስቦ ውሏል።ይህንን እንደ ሕዝብ የእኩልነት ቀን አድርጎ የሚቆጥረው ቡድን የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ፣ኢትዮጵያ አንድነቷን ያረጋገጠችበት ቀን ነው ሲል ቀጣፊው አብይ አህመድ ንግግር አድርጓል።ይህ ሕዝቡን የመናቅና አገሪቱም ያለችበትን የመበታተን አደጋ የካደ ንግግር መሆኑን እንኳንስ ኢትዮጵያዊ ቀርቶ የውጭ አገር ዜጋም ቢሆን የሚመሰክረው ሃቅ ነው።አብይ እንዳለው ሕገ ጥፋቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ እኩል አደረገ?ኢትዮጵያንስ አንድ አደረጋት?ታዲያ ቀደም ሲልና አሁንም ድረስ ሕገመንግሥቱ ይወገድ ወይም ይሻሻላል የሚለው ጥያቄ ለምን ተነሳ?አብይስ ይሻሻላል የሚል ተስፋ ለምን ሰጠ?ምን ይህል የኢትዮጵያን ሕዝብ ቢንቀው ነው እንዲህ የዘላበደው? እንደኛ ከሆነ ሕገ ጥፋቱ ሌቦችና ጎሰኞችን ያስተባበረ ቃል ኪዳን ነው።አገር ለማፍረስ የተስማሙ ቡድኖች የተፈራረሙበት ሰነድ ነው።ተቀዳዶ መጣልና በሕዝብ ተሳትፎና ፍላጎት ላይ በተመሰረተ የዜጎችን መብት፣ያገርን አንድነትና ልዑላዊነት በሚያረጋግጥ ሕገ መንግሥት መተካት አለበት ።

ብረት እንደጋለ ይባላልና የተጀመረው ትግል ከዳር እንዲደርስ ሁሉም እንዲሳተፍበት፣ በተነሳሳው የሕዝብ ትግል ላይ ውሃ ለማፍሰስ የሚሞክሩ ካሉ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ጥሪ እናደርጋለን።ቆሎን መቆርጠሙ እንጂ ማሹቱ አይፈጀውም!በተመሳሳይም ችግሩን ማንሳት ብቻ አያሶግደውም።ችግሩ የሚወገደው ችግር ፈጣሪ የሆነው ሲወገድ ብቻ ነው።መብት የሚረጋገጠው በልመና ሳይሆን በቆራጥ ትግል መሆኑን ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል።

ማሳሰቢያ ለአማራው ከአማራው በላይ ጠበቃ በመሆን ፤ለኢትዮጵያም አንድነትና ልኡላዊነት ሽንጡን ገትሮ የሚከራከረው አንጋፋው ጋዜጠኛና የታሪክ ተመራማሪ አቶ ታዴዎስ ታንቱ አሁንም በእስር ቤት ውስጥ እዬተሰቃዬ ይገኛል።ይህንን ጀግናና እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጅ ማዳን የሁሉም አገር ወዳድ ግዴታ ነው።ሁላችንም ፍትሕ ለታዲዎስ ታንቱ ብለን መጮህ አለብን።

ጥንቅራችንን በአቶ ሃይሉ ገ/ዩሃንስ(ገሞራው )የቀደመ ምክር እናጠቃልላለን

ያሰብከው ባይሰምር ሁኔታው ቢጠጥር

ጠባሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር

አዎ ከባዱንና መጥፎውን የመከራ ፈተና በጥንካሬና በጥበብ ካላለፉት በጎ ነገር አይገኝም፤ካሰቡበት ቦታም  መድረስ አይቻልም።

የአንድነት ግንባር ይመሥረት፣የጎሰኞች ፖለቲካና አስተሳሰብ ይወገድ!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘላለም ትኑር!!